# በኦንላይን በተገኘ የአሸባሪዎች ድጋፍ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን ማስሰረዝ አይቻልም !!

ኢብሳ ነመራ 01/17/14

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ከሕዝብ ልብ ውስጥ መጥፋቱን ሲረዳ ድንገት እጁ ውስጥ የገባ አጀንዳ ይዞ ማራገብ ዋነኛ መገለጫው ነው፡፡ ይህ ባህሪው የተለመደ ከመሆኑ የተነሣ መለያው ለመሆን በቅቷል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ ከስድስት ወራት በፊት "ሕዝባዊ ንቅናቄ" በሚል የፀረሽብርተኝነት ሕጉን ለማሰረዝ የአንድ ሚሊየን ሰዎች ፊርማ አሰባስባለሁ ማለቱ ይታወሣል፡፡ አንድነት ይህን ያደረገው አለሁ ለማለት እንጂ በወከባና ከተወሰኑ ቡድኖች ፊርማ በማሰባሰብ ሕግ ማስለወጥ እንደማይቻል ጠፍቶት አይደለም፡፡ ይህ ባይጠፋውም፣ ከስድስት ወር ጭው ያለ ቆይታ በኋላ ሠሞኑን ከተዘነጋ/ከተረሳበት "የፀረሽብር ሕጉን ለማሻር የአንድ ሚሊዮን ሠዎች ፊርማ አሰባስቤ ጨርሻለሁ አትርሱኝ" በማለት ብቅ ብሏል፡፡

አንድነት ፓርቲ የፀረሽብርተኝነት ሕጉ እንዳልተመቸው መናገር የጀመረው አሁን አይደለም፡፡ ይህ የአንድነት አቋም ብዙዎቹን ግራ ሲያጋባ ቆይቷል፡፡ በይፋ እስከምናውቀው ድረስ አንድነት አሸባሪ ፓርቲ አይደለም፡፡ "አሸባሪ ሣይሆን የፀረሽብር ሕጉን ይህን ያህል የፈራውና ሥጋት የፈጠረበት ምክንያት ምንድነው ነው?" የሚለው ነው ብዙዎችን ግራ ያጋባው፡፡ ብዚህ ሳቢያ "አንድነት ስውር አጀንዳ ይኖረው ይሆን?" ብለው የተጠራጠሩ ያሉትን ያህል ሕጉን በተመለከተም "ስለእውነት ለመነጋገር፣ የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም? አሸባሪ ያልሆኑ አካላትን የሚያሰጋ ነው? ይህን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀን ሕግ የተወሰኑ ሰዎችን የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ እንዲሠረዝ ማድረግ ይቻላል?" የመሳሰሉ ጥያቄዎች በህሊናቸው የተመላለሱባቸው ሰዎች አልታጡም፡፡

በቁም ትርጉሙ፣ አንድነት "የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ለኢትዮጵያ አያስፈልጋትም" በሚል የያዘው አቋም "ኢትዮጵያ ውስጥ ፈፅሞ የሽብር ሥጋት የለም" የሚል የማያሻማ

መልዕክት አለው፡፡ እውነት ለመናገር ባለፉት ሁለት አሥርት አመታት የሽብር ጥቃት ሰለባ በመሆን ኢትዮጵያ ቀዳሚ የዓለማችን ሃገር ነበረች፡፡ ከ1987 ዓ/ም ወዲህ ባሉት አመታት ራሱን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ብሎ የሚጠራው አሸባሪ ቡድን በአዲስ አበባና በሌሎች የአገሪቱ ከተሞች በፈፀማቸው የሽብር ጥቃቶች 53 ንፁሀን ሰዎች ሞተዋል፤ 253 ደግሞ አካላቸው ጎድሏል፡፡ በተመሳሳይ ራሱን የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ብሎ የሚጠራው አሸባሪ ቡድን በአዲስ አበባና በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በፈፀማቸው የሽብር ጥቃቶች 283 ንፁሃን ሰዎች ሞተዋል፤ 110 አካላቸው ጎሏል፤ 25 ጠለፋ ተፈፅሞባቸው እስካሁን የደረሱበት አይታወቅም፡፡ አልሸባብና ግንቦት 7 በተለያየ ግዜ አስከፊ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የሽብር ጥቃቶችን ለመፈፀም አቅደው በፀጥታ ሃይሎች ብርቱ ክትትል ከሽፎባቸዋል፡፡

አንድነት የፀረሽብርተኝነት ሕጉን እሠርዛላሁ ካለበት ከመስከረም 2006 ዓ/ም ወዲህ ባለው ጊዜ ውስጥ እንኳን የአልሸባብ አጥፍቶ ጠፊዎች ጥቅምት 3 የኢትዮጲያና የናይጄርያ ብሄራዊ የእግር ኳስ ቡድኖች በሚጫወቱበት ዕለት አስከፊ ጥፋት ሊያደርስ ይችል የነበረ የሽብር ጥቃት ለመፈፀም ሙከራ አድርገው ከሽፎባቸዋል፡፡

እነዚህ የንፁሀን ዜጎቻችንን ሕይወት የበሉና ስጋት እየፈጠሩ ያሉ የሽብር ጥቃቶች በግለሰቦች መሃከል ባለ አለመግባባት፣ በቂም በቀል፣ በጊዜያዊ ግጭት ደም ፍላት ወይም ለዘረፋ ዓላማ የተፈፀሙ ተራ የነብስ ግድያ ወንጀሎች አልነበሩም፡፡ በመጠጥና በአደንዛዠ እፅ ስካር በመገፋፋት የተፈፀሙ የነብስ ማጥፋት ድርጊቶችም አልነበሩም፡፡ ከዚህ ይልቅ ሕዝብንና መንግስትን በማስፈራራት ርዕዮተ ዓለማዊና ሃይማኖታዊ ዓላማን በኃይል ማሣካትን ያለመ፣ ድርጊቱን በጥንቃቄ ያቀነባበሩ መሪዎች ያሉት፣ አላማቸውን ለማስፈፀም የሚያስችል መዋቅር ተዘርገቶና የፀጥታ አስከባሪዎችን እንቅስቃሴ ታሣቢ ባደረገ ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን የተፈፀሙ ወንጀሎች ናቸው፡፡ተራ የወንጀልና ድርጊቶች ሣይሆኑ ድርጅታዊ መዋቅር ያላቸው ረቂቅ ወንጀሎች ናቸው፡፡

የአንድነት አመራሮች የሽብር ጥቃት በራሣቸው ላይ ወይም በቤተሰባቸው አባል ላይ ስላልደረሰ ብቻ "አላየነውም፣ ኢትዮጵያ የሽብር ወንጀል ሥጋት የለባትም" በሚል

በሚያስገርም ሁኔታ ክህደት የፈፀሙት፤ ከዚህም አልፈው "ሥጋቱ ኢህአዴግ ጋር ብቻ ነው ያለው" እያሉ ኃላፊነት በጎደለው ሁኔታ የሚያንጓጥጡት ከላይ የተገለጡት የሽብር ጥቃቶችን ችላ ብለው ነው፡፡

የሽብርተኝነት ድርጊት የትና መቼ እንደሚፈፀም አስቀድሞ ማወቅ አይቻልም፡፡ የሽብርተኝነት ድርጊት ከመደበኛም ሆነ ከደፈጣ ጦርነት ውጊያዎች በተለየ መምጫውም ሆነ የሚካሄድበት አቅጣጫው አይታወቅም፡፡ የጥቃት ዒላማዎቹ መሣሪያ የታጠቀ የመከላከያ ወይም የፖሊስ ሠራዊት አይደሉም፡፡ ተግባሩ ዒላማ የሚያደረገው፣ ራሣቸውን ከጥቃት የመከላከል አካላዊ ብቃት የሌላቸው ሕፃናትንና አዛውንትን ጨምሮ ፍፁም ሠላማዊ ዜጎችን ነው፡፡ የሽብር ድርጊት ውጤታማነት የሚለካውም በእነዚህ ፍፁም ሠላማዊ ዜጎች ላይ ባደረሰው የሕይወት ሞትና የአካል መጉደል መጠን ነው፡፡ ይህ የሆነው ሕዝብ ሊፈፀምበት የሚችለውን የሽብር ጥቃት በማስፈራት መንግሥት ላይ ጫና እንዲያሣድር፤ መንግሥትም የህይወትና አካላዊ ደህንነታቸውን፣ በሠላም ወጥቶ የመግባት ዋስትናቸውን የመጠበቅ ሃላፊነት ስላለበት፣ ይህን አደራ በሠጡት ዜጎች ላይ የከፋ ጉዳት ሲደርስ፣ ዜጎች ከሚጎዱ በሚል እንዲንበረከክ የማድረግ አጥፊ ሥልት ስለሚከተል ነው፡፡

በመሆኑም ሽብርተኝነት ከሌሎች ወንጀሎች ሁሉ የተለየ ባህሪ ያለው፣ ለቁጥጥርና ሕጎዊ እርምጃ ለመውሰድ አሰቸጋሪ፣ ውጤቱም እጅግ አስከፊ የሆነ አደገኛ ወንጀል ነው፡፡ ከሌላ ወንጀል በተለየ ልዩ ክትትል፣ የምርምራ ሂደትና ቅጣት የሚፈልግ ወንጀል ነው፡፡ የሽብርተኝነት ወንጀል በሚል የተለየ ሕግ ማውጣት ያስፈለገውም ለዚህ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፣ ኢትዮጵያ በተጨባጭ የሽብር ጥቃት ሰለባ ስለሆነችና አሁንም አሸባሪ በሚል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተፈረጁ ቡድኖች የሽብር ጥቃት ለመፈፀም ዛቻ እየሰነዘሩ በመሆኑ የህዝቡን ሰላምና ፀጥታ፣ ሕገመንግስታዊ ሥርአቱን ለመጠበቅ የፀረ ሽብርተኝነት ሕግ የግድ ያሰፈልጋታል።

ከዚህ በተጨማሪ በተለይ ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ማገባደጃ በኋላ የሽብርተኝነት ድርጊት ዓለም አቀፋዊ ገፅታን እየላበሰ መጠቷል፡፡ በ1989 ዓ/ም በኬንያና በታንዛኒያ የአሜሪካ ኤምባሲ ጽ/ቤቶች ላይ የፈተፀሙት የሽብር ጥቃቶች፣ የሴፕተምበር 11 የአሜሪካ የንግድ ማእከል ህንፃ ላይ የፈተፈፀመው የሽብር ጥቃት፤ በእንግሊዝ፣ በሩሲያ . . .. የተፈፀሙ

ተመሳሳይ ጥቃቶች እንዲሁም በይፋ የሚነገሩ ዛቻዎች የሽብርተኝነት ጥቃት የዚያ ወይም የዚህ አገር የተናጠል ችግር ሳይሆን የዓለም ሃገራት ሁሉ ሥጋት እንዲሆን አድርገውታል።

ከጉዳዩ አሳሳቢነትም በመነሳት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአውሮፖ ህብረትና የአፍሪካ ሕብረት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጡ፡፡ ዓለም አቀፍ መረብ ያለውን ሽብርተኝነት ለመከላከል አባል አገሮቻቸው ሽብርተኝነትን መከላከልና አሸባሪዎች ላይ አስተማሪ የሆነ ቅጣት ማሣለፍ የሚያስችል ሕግ እንዲያወጡ ሥምምነት ላይ ደረሱ፤ አስገዳጅ ሥምምነት፡፡ የኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ሕግ መግቢያ ላይ አዋጅን ማውጣት ያስፈለገበትን ምክንያ "ሽብርተኝነትን በሚገባ ለመዋጋት የፀረሽብርተኝነት ዓላማ ካላቸው የአካባቢያችን፣ የአህጉራችንና የሌላው የዓለም ክፍሎች መንግሥታትና ሕዝቦች ጋር መተባበርና በተለይ ከተባበሩት መንግሥታትና ከአፍሪካ ሕብረት አባል ሀገራት ጋር የተደረጉትን ሥምምነቶች ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊነቱ የታመነበት በመሆኑ፤" የሚል መስፈሩም ለዚሁ ነው፡፡

እንግዲህ አንድነት እንደተራ ነገር ቆጥሮ በኦንላይን ጭምር ሠበሰብኩት ባለው የ1 ሚሊዮን ሠዎች የድጋፍ ድምጽ "አሠርዘዋለሁ" የሚለው ከላይ በተጠቀሱት መሠረታዊ እውነታዎች ላይ ተመስርቶና አስፈላጊነቱ በተጨባጭ ታምኖበት የአገሪቱ ከፍተኛ የሥልጣን አካል በሆነው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀውን የፀረ ሽብርተኝነት ህግ ነው፡፡ አንድነት በዚህ አቋሙ በንፁሃን ኢትዮጵያን ላይ የደረሰው ዘግናኝ የሽብር ጥቃት ምንም እንዳላሳሰበው በግልፅ አሳይቷል፡፡ ለወደፊት ሊደርስ የሚችለውም ዘግናኝ የሽብር ጥቃት ምንም አላሣሠበውም፡፡ ታዲያ፣ ይህን ፓርቲ የሕዝብ ወገንተኝነት ያለው ቅን ፓርቲ ነው ብሎ መደምደም፣ አይደለም መደምደም ማሰብስ ይቻል ይሆን?

የአንድነት አመራሮች "የሽብር ሥጋት ያለው ኢህአዴግ ጋር ብቻ ነው" እያሉ ሲያላግጡ ሰምተናል፡፡ እርግጥ ነው ኢህአዴግ "የሽብር ሥጋት አለ፤ ሕዝቡ ውስጥም ሥጋት አለ፡፡" ብሎ ያምናል፡፡ ሥጋቱ ከምንም የመነጨ ሣይሆን በተጨባጭ በአገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ከደረሱና ሊደርሱ ከሚችሉ ጥቃቶች የመነጨ ነው፡፡ ኢህአዴግ ሕዝባዊ ወገንተኝነት ስላለው፣ እንደገዢ ፓርቲም የሕዝቡን ደህንነት የመጠበቅ ኃላፊነት ስለተጣለበት የሕዝቡን ሥጋት ይጋራል፡፡ የህዝቡን ደህንነት ከሽብር ጥቃት ለመከላከልና

አጥፊዎቹም ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ እንደገዢ ፓርቲ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት የፀረሽብርተኝነት ሕጉ እንዲወጣ አድርጓል፡፡

አንድነት "የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉ አያስፈልገንም" ሲል ለዚህ ያቀረበው ምክንያት "በአገሪቱ የሽብር ሥጋት የለም" የሚል ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህ ጋር "የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ራሱ አሸባሪ ነው" የሚል አቋም እንዳለው ከፍተኛ አመራሮቹ በይፋና በተደጋጋሚ ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡ የአንድነት አመራሮች "የፀረሽብርተኝነት ሕጉ አሸባሪ ነው" ሲሉ፣ "ሽብርተኝነት (terrorism)" ለሚለው እሳቤ የተሰጠውን አገራት የተስማሙበትን መደበኛ ፍቺ ታሳቢ ያደረገ አይመስለኝም፡፡ የአንድነት አመራሮች ይህን ሲናገሩ ለድርጊቱ የተሰጠውን መደበኛ ፍቺ በማስታወስም አይደለም። እስካሁን ባለው መረጃ፣ ተቀባይነትን ያገኘ መደበኛ (conventional) የሽብርተኝነት ድርጊት ፍቺ በአጭሩ፣ "ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተ አለማዊ ወይም ሃይማኖታዊ ዓላማን ለማሳካት በንፁሃን ዜጋ ላይ ግድያ፣ አፈና፣ ማስፈራሪያና መሰል ጥቃቶችን መፈፀም" የሚል ነው፡፡

የኢትዮጵያ የፀረሽብርተኝነት ሕግ አንቀፅ 3 የሽብርተኝነት ድርጊትን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፤

*ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን የፖለቲካ፣ የሃይማኖታዊ ወይም የአይዲዮሎጂ ዓላማን ለማራመድ በማሰብ በመንግስት ላይ ተፅዕኖ ለማሣደር ሕብረተሰቡን ወይም የሕብረተሰቡን ክፍል ለማስፈራራት ወይም የሃገሪቱን መሠረታዊ ፖለቲካዊ፣ ሕገመንግሥታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ ተቋማትን ለማናጋት ወይም ለማፍረስ፤*

1. *ሰውን የገደለ ወይም በአካሉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ ፣*
2. *የሕብረተሰቡን ወይም የሕብረተሰቡን ክፍል ደህንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣*
3. *እገታ ወይም ጠለፋ የፈፀመ፣*
4. *በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ፣*
5. *በተፈጥሮ ሃብት፣ በአካባቢ፣ በታሪካዊ ወይም የባህል ቅርስ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰ፣*
6. *ማናቸውንም የሕዝብ አገልግሎት ለከፍተኛ አደጋ ያጋለጠ፣ የያዘ፣ በቁጥጥር ሥር ያደረገ፣ ያቋረጠ ወይም ያበላሸ፣ ወይም*
7. *በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 6 ከተመለከቱ ድርጊቶች መሃከል ማናቸውንም የመፈፀም፣ የዛተ*

እንግዲህ አንድነት “የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን አሸባሪ ነው” ሲል “ሕጉ እነዚህን ድርጊቶች ለመፈፀም እየዋለ ነው” እያለ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ምክንያቱም የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉ ባልታሰበ ስፍራና ቦታ ፈንጂ በማጥመድና ፈንጂ የታጠቁ አጥፍቶ ጠፊዎችን በማሰማራት የንፁሃን ሰዎችን ሕይወት እንዲጠፋ አያበረታታ ብቻም ሳይሆን ጭራሽ እንዲዘናጉ አያደርግም ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአንድ ነገ ስልጣን ተረክቤ አገር እመራለሁ ከሚል ፓርቲ ባልተጠበቀም ነበር። እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር አለ፤ እሱም አንድነት “የፀረሽብርተኝነት ሕጉ አሸባሪ ነው” ሲለን “ሕጉ አላላውስ ያላቸው፣ ያራዳቸው ቡድኖችና ግለሰቦች አሉ” እያለን መሆኑን በግልፅ እንረዳለን፡፡

እዚህ ላይ እርግጥ *የፀረ ሽብር ሕጉን የሚፈሩ ሰዎች አሉ? እነሱስ እነማን ናቸው?* የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ አዎ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን የሚፈሩ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉ። ሕጉ ንፁሃን ሰዎችን፣ ሕፃናትንና አዛውንትን ሳይለይ ባላሰቡት ስፍራና ግዜ ህይወታቸውን በመቅጠፍ ፍርሃት እንዲነግስ በማድረግ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ዓላማቸውን የማሳካት እንቅስቃሴያቸውን የሚገድብባቸው፣ ውጥናቸውን የሚያከሽፍባቸው፣ የሽብር ጥቃት ሲሞክሩና ፈፅመው ሲገኙ አስተማሪ የሆነ ቅጣት እንደሚያከናንባቸው የሚያውቁ ቡድኖችና ግለሰቦች ሕጉን አይወዱትም፤ ይፈሩታልም፡፡ ለምሳሌ ከዚህ ቀደም ለበርካታ ንፁሃን ዜጎች ሕይወት መጥፋት፣ አካል መጉደል፣ ንብረት መውደም ምክንያት የሆኑት  የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻ አውጭ ግንባር (ኦብነግ)፣ ግንቦት 7፣ አል ሸባብ . . . የፀረ ሽብር ሕጉ እንዳይንቀሳቀሱ ስላገዳቸውና ከዚህ በፊት በፈፀሙት ድርጊት ሳይቀር ሕግ ፊት እንደሚያቀርባቸው ስለሚያውቁ ይፈሩታል፡፡

ሰላማዊ ዜጎችና ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቀሴ ውስጥ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሙሉ ከእነዚህ አሸባሪዎች ጥቃትና ሥጋት ነፃ የመሆን ጥብቅ ፍላጎት አላቸው። በመሆኑም ሕጉን አይፈሩትም፣ አያሸብራቸውምም፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ አንድም ሰላማዊ ዜጋ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን ፈርቶ አያውቅም።  ከአንድነት በስተቀር፡፡ ብዙዎችም አንድነት የፀረሽብርተኝነት ሕጉን ለምን አጥብቆ እንደሚፈራ ግራ ገብቷቸዋል፤ ፓርቲውንም በስሱ የተጠራጠሩ አልጠፉም፡፡ እርግጥ፣ አንድነት ሕጉን ለመቃወሙ ምክንያት ያላቸውን አንዳንድ ነገሮች አልፎ አልፎ ጠቀስ ሲያደርግ

ይደመጣል፡፡ ይህም "ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴንና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትን ይገድባል" የሚል ነው፡፡ ሕጉን በወጉ ስንመረምር ግን አንድም የዚህ አይነት ተገቢ ያለሆኑ የመብት ጥሰቶች እንዲፈፀሙ የሚያደርግ ክፍተት የለውም፡፡ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የፀረሽብር ሕጉ በአንቀፅ 3 ላይ የሽብርተኝነት ድርጊትን በተመለከተ ባስቀመጠው ድንጋጌ ሰላማዊ የሆነ ግለሰበ ወይም ቡድን ከሽብርተኝነት ድርጊት ጋር የሚጣረስበት አንድም የተምታታ ሃሳብ የለውም። ካለም ማሳየት ይቻላል።

አንድነት ሲጋት በማለት ወዳስቀመጠውም ስንመለስ ፀረ-ሽብር ሕጉ ፕሬስን በተመለከተ በአንቀፅ 6 ላይ ያሰፈረውን ድንጋጌ እናገኛለን፡፡ ይህ አንቀፅ "ማንኛውም ሰው መልዕክቱ **እንዲታተምላቸው የተደረገው የሕብረተሰብ አባላት** በከፊል ወይም በሙሉ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 3 (የሽብርተኝነት ድርጊቶች) ማናቸውንም የሽብርተኝነት ድርጊት እንዲፈፅሙ ወይም ለመፈፀም እንዲዘጋጁ ወይም እንዲነሳሱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያበረታታቸው ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ የሚገፋፋቸው እንደሆነ **አድርገው ይረዱታል** ተብሎ ሊገመት የሚችል መልዕክት ሆን ብሎ ወይም በግድየለሽነት ያተመ ወይም ያሳተመ . . ." ሽብርተኝነትን በማነሳሳት ወንጀል እንደሚጠየቅ ይደነግጋል፡፡

በዚህ አንቀፅ ላይ የሰፈረው ሃሳብ ይዘት፣ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ቡድን ሃይማኖታዊ ወይም ርዕዮተ አለማዊ ዓላማውን ለማሳካት፤ ሰውን እንዲገድል፣ በሰዎች አካል ላይ ጉዳት እንዲያደርስ፣ ከእርሱ ውጪ ነው ብሎ ያሰበውን የሕብረተሰብ ክፍል ደሕንነት ወይም ጤና ለከፍተኛ አደጋ እንዲያጋልጥ . . . ወይም እንዚህን ድርጊቶች ለመፈፀም እንዲነሳሳ የሚያደርግን መልእክት በፕሬስ አማካኝነት ማስተላለፍ ሽብርተኝነትን ማበረታታት ነው፣ ሽብርተኝነትን በማበረታታት ወንጀል ያስጠይቃል፣ ያስቀጣልም የሚል ነው፡፡

ሃሳብን የመግለፅ ወይም የፕሬስ ነፃነት የሌሎችን ሰብአዊ መብትና ሰብአዊ ክብር መጣስንና እንዲጣስ ማበረታታትን አያጠቃልልም፡፡ እናም የፕሬስ ውጤትን ለአስከፊ የሰብአዊ ምብት ጥሰት ምክንያት የሆነን የሽብተኝነት ድርጊት ለማበረታታት መጠቀም በወንጀል ያስጠይቃል፡፡ እናም "ፕሬስን ለዚህ ዓላማ መጠቀም በወንጀል ያስጠይቃል" ተብሎ መደንገጉ ተገቢና ፍትሃዊ ነው፡፡ ይህ አንድነት "የፀረሽብርተኝነት አዋጁ የፕሬስ

ነፃነትንና የጋዜጠኞችን መብት ይገድባል" በሚል የያዘው አቋም መሰረተ ቢስ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንግዲህ አንድነት ለኢትዮጵያ አስፈላጊ፣ ፍትሃዊና ተገቢ የሆነውን የፀረሽብርተኝነት ሕግ ነው አሰርዛለሁ እያለ የሚያቅራራው፡፡ ምን ያለበት ምን አይችልም እንዲሉ ካልሆነ በስተቀር፣ ለኛ ፀረ-ሽብርተኝነት ህጉ እጅግ ያስፈልገናል።

ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ "የፀረ ሽብር ሕጉን ለማሰረዝ ፊርማ ማሰባሰብ ጀምሬያለሁ" ብሎ ከነገረን ከሰባት ወራት በላይ ተቆጥረዋል፡፡ "በሰላማዊ ሰልፎች መንግስትን አውካለሁ፣ አደናግራለሁ" በሚል ሕዝባዊ ንቅናቄ መጀመሩን የነገረን ሰሞን ነበር ፊርማ እንደሚያሰባስብ ያሳወቀን፡፡ ታዲያ ሰልፎቹ ሰሚ አጥተው ጥቂት ሰዎች የተንጫጩበት የደሃ ሰርግ መስለው ማብቃታቸውን የተመለከቱ፣ ፊርማ ማሰባሰቡም እንደዚሁ በወሬ መቅረቱን አውቀው ነበር፡፡ አንድነት ግን ጉዳዩ ከተረሳና ይደርሳል ከተባለበት ግዜ በአራት ወር ገደማ ዘግይቶ ፊርማ አሰባስቦ መጨረሱን ሰሞኑን ነገረን፡፡ ፊራሚዎቹን ወይም ድጋፉን በአካል ሳይሆን ብቻ ሳይሆን በኦንላይን (በኢንተርኔት) ማሰባሰቡንም ነግሮናል፡፡ (በኦንላይን የተሰጠ ድምፅ፣ የድምፅ ሰጪውን ማንነት ማወቅ እንደማይቻል ልብ በሉ፡፡)

በርካታ ኢትዮጵያውያን፣ በኦንላይን "የፀረሽብርተኝነት ሕጉ ይሰረዝ" ብለው ድጋፍ የሰጡት ሰዎች የፀረ-ሽብር ሕጉ አላላውስ ያላቸው የሸአቢያ ተላላኪዎች፣ የአልሸባብ፣ ኦነግና ኦብነግ ጀሌዎች መሆናቸውን ገምተዋል፡፡ እናም አንድነት የአሸባሪዎች ድጋፍ ላይ ተመስርቶ ነው የፀረ ሽብር ሕጉን አሰርዛለሁ የሚለን፡፡ ይህም አንድነት የሚሰራውን የማያውቅ፣ መንግስትን ለመቃወም የሚያመቸው መስሎ ከታየው አገርን ለባዕድ ጠላት አሳልፎ ከመስጠትም የማይመለስና ፍፁም ሃላፊነት የማይሰማው ፅንፈኛ ፓርቲ መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡

ይሁን፣ አንድነት የ1 ሚሊየን ሰዎችን ፊርማ ወይም ድጋፍ አግኝቷል እንበል፡፡ በዚህ የድጋፍ ፊርማ ሕግ ማሻር ይቻላል ወይ? አንድ ሰው እንደ ሺ ሆኖ የሚሞላው የኦንላየን ድምፅ ሕግ ማሻር የሚያስችል ሕገመንግስታዊ መብት አለው ወይ? ወደ እውነታው ስንመጣ የምንረዳው ቁም ነገር ቢኖር፣ አንድነት ይህን ለማድረግ የሚያስችለው አንድም ሕጋዊ መሰረት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ሕግ የሚወጣው፣ የሚሻረው ወይም የሚሻሻለው

በሕዝብ ውክልና በተሰየመ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብቻ ነው፡፡ የምክር ቤቱ አባላት በሕገመንግስቱ መሰረት ሕግ እንዲወጣ፣ እንዲሻሻል . . . ሃሳብ ማመንጭጨት፣ የውሳኔ ሃሳብ (ሞሽን) ማቀረብ ይችላሉ፡፡ የመነጨው ሃሳብ ወይም የቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ሕግ የሚሆነው ግን በምክር ቤቱ አብላጫ ድምፅ ብቻ ነው፡፡ በአገራችን ኢትዮጵያ ህግ የሚወጣበትና የሚሻሻልበት አግባብ ይህ ብቻ ነው፡፡ አንድነቶች ይህን ከልባቸው ልብ ሊሉት ይገባል።

አንድ ሕግ፣ የህግ አንቀፅ ፣ ወይም ውሳኔ ሕገመንግስቱን ይፃረራል የሚል አቋም ያላቸው ወገኖች "ይፃረራል" ብለው ያመኑበትን ድንጋጌ እንዲሻሻል የሚያደርጉት ፊርማ በማሰባሰብ ሳይሆን፣ ጉዳዩን ሕገመንግስቱን የመተርጎም ስልጣን በሕገመንግስቱ ለተሰጠው የሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ተወካዮች ለሚገኙበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በማቅረብ ነው፡፡ ፍርድ ቤት ወይም ሌላ ተቋም ይህን የማድረግ ሕገመንግስታዊ ስልጣን የለውም፡፡ እናም አንድነት ማንነታቸውን፣ ዜጎች ይሁኑ አይሁኑ የማያውቃቸውን "በኦንላይን ድጋፍ ሰጡኝ" ያላቸውን ሰዎች መነሻ አድርጎ "የፀረሽብርተኝነት ሕጉን ለማሻር ጉዳዩን ወደፍርድ ቤት እወስደዋለሁ" የሚለው አካሄዱ ምንም ሕጋዊ መሰረት የሌለው "ሕዝብን ለማደናገር ይጠቅማል" ከሚል ከተለመደውና ከሰለቸን የፓርቲው አመራሮች ከንቱ እምነት የመነጨ ነው፡፡

የአንድነት ፓርቲ አመራሮች፣ ሕግ ለማሻር የ1 መቶ ሺሕ፣ የ1 ሚሊየን ሰዎች ድጋፍ አለን ሲሉ በአብላጫ ድምፅ የመንግስት ስልጣን የተረከበውና የአገሪቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል የሆነው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጀርባው በሃያዎቹ ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ለአካለ መጠን የደረሱ ኢትዮጵያውያን ያሉ መሆናቸውን መዘንጋት የለባቸውም፡፡ እርግጥ አንድነት "ምረጡኝ፣ የስልጣን ውክልና ከሰጣችሁኝ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን እሰርዘዋለሁ" ማለት ይችላል፤ ጉዳዩን የምርጫ መወዳደሪያ አጀንዳ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ይሄኔ አቋሙ የሚያስከትለውን ውጤት ያውቀዋል፡፡

ባጠቃላይ፣ አንድነት በኦንላይን ባሰባሰበው የሽአቢያ፣ የአልሸባብና ሌሎች የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የፈረጃቸው ቡድኖች ጀሌዎች ድጋፍ፣ የፀረ ሽብርተኝነት ሕጉን አሰርዛለሁ እያለ መድከሙም ሆነ ሳይታክት የሚነዛው ወሬ ምንም ሕጋዊና ሞራላዊ

መሰረት የሌለው ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ መሆኑ በውል መታወቅ አለበት፡፡ ለማንኛውም በኦንላይን በተገኘ የአሸባሪዎች ድጋፍ የፀረሽብርተኝነት ሕጉን ማስሰረዝ እንደማይቻል ለአንድነትም ሆነ ለሌሎች ተመሳሳይ አላማ ላላቸው (ካሉ) ወገኖች በድጋሚ ማስታወስ፣ ያስቡበትም ዘንድ ማሳሰብ ተገቢ ይሆናል፡፡